የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት
THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA
OFFICE OF THE FEDERAL
AUDITOR GENERAL

ቁጥር OFAGF.03.24
ቀን 02/08/201

ለክብርት ወ/ሮ አለምፀሐይ ጳውሎስ
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ኃላፊና
የካቢኔ ጉዳዮች ሚኒስትር
ለክቡር ኢንጅነር ወርቁ ጋቸና
የአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር
<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ፡- <u>የአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ውጤትና አስተያየትን ይመለከታል</u>

በርዕሱ የተጠቀሰውን የአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት የ2014 በጀት ዓመት የኦዲት ውጤትና አስተያየት የያዘ 12 ገጽ የኦዲት ሪፖርት እና 12 ገጽ የሂሣብ ሪፖርቶች በድምሩ 24 ገጽ የያዘ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ አድርገን የላክን መሆኑን እንገልጻለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

አበራ ታደሰ
የፌዴራል ም/ዋና ኦዲተር

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት
THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA
OFFICE OF THE FEDERAL
AUDITOR GENERAL

ቁጥር OFAGF-03,24/12/5
ቀን 02/08/2015

ለክብርት ወ/ሮ አለምፀሐይ ጳውሎስ
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ኃላፊና
የካቢኔ ጉዳዮች ሚኒስትር
ለክቡር ኢንጅነር ወርቁ ጋቸና
የአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር
<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ፡- <u>የአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ውጤትና አስተያየትን ይመለከታል</u>

በርዕሱ የተጠቀሰውን የአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት የ2014 በጀት ዓመት የኦዲት ውጤትና አስተያየት የያዘ 12 ገጽ የኦዲት ሪፖርት እና 12 ገጽ የሂሣብ ሪፖርቶች በድምሩ 24 ገጽ የያዘ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ አድርገን የላክን መሆኑን እንገልጻለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

አበራ ታደሰ
የፌዴራል ም/ዋና ኦዲተር

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

የአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት

የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ

የኦዲት ሪፖርት

መጋቢት/2015 ዓ.ም

አዲስ አበባ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት

የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ

ኦዲት ሪፖርት

የአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት የተመደበለትን የመደበኛና የካፒታል ሂሳብ በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፣ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መያዙንና የመንግሥት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል።

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን ሲሆን፣ ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው። እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል። ኦዲታችን ፦

- በሂሳብ ሪፖርቶች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ ሪፖርቶችን ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል።

ከዚህም በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይጨምራል::

የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል።

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት የአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፣ መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች፣ እንዲሁም በኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው:: ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው::

የሚከተሉት የአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት የሂሳብ ሪፖርቶች፣

- የገቢ/የዕርዳታ/የብድር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የሂሳብ ሚዛን ሙከራ፣

ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል::

__ለኦዲት አስተያየቱ መሠረት የሆኑት ጉዳዮች(Basic of Audit Opinion)፣__

የአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን የጠበቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

1. __በጀት ዓመቱን ያልጠበቀ ክፍያ፣__

   የፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የመደበኛና ካፒታል የስራ ማስኬጃ ወጪዎች ሲፈጸም ወጪዉ ለሚደረግበት ተግባር በበጀት ዓመቱ የተያዘ ወይም ወጪዉን ለመሸፈን ቀሪ በጀት መኖሩንና ወጪዉ በመስሪያ ቤቱ ዕቅድ ውስጥ የተያዘና በጥሬ ገንዘብ ፍላጎት ላይ የተካተተ መሆኑ ሳይረጋገጥ ወጪ መፈፀም እንደማይገባ መመሪያው ይገልፃል:: በዚህም መሰረት የኢንስቲትዩቱ የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ በናሙና ኦዲት ሲደረግ፣ በቀን 22/11/2013 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 727467 በሂሳብ መደብ 6252 ብር 502,706.40 በ2013 በጀት ዓመት መከፈል የነበረበት የሰኔ ወር የተሽከርካሪ ኪራይ ክፍያ አገልግሎቱ በተገኘበት በጀት ዓመት መክፈልና ማወራረድ ሲገባው ወይም በ2014 በጀት እንደሚከፈል በተከፋይ ሂሳብ ሳይያዝ ያለ በጀት አመቱ በ2014 በጀት ዓመት ክፍያ በመፈጸሙ የወጪ ሂሳብን ያለአግባብ ከፍ እንዲል ያደረገው መሆኑ በኦዲት ተረጋግጧል::

2. __ያለ ሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ደረሰኝና የባንክ አድቫይስ ያልቀረበለት ክፍያ፣__

   የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 608/2001 አንቀፅ 91 ሀ/2 መሰረት ማንኛውም በሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ የመጠቀም ግዴታ ያለበት ተቋም የሽያጭ መሳሪያው በጥገና ላይ ባለበት ጊዜ ካልሆነ በስተቀር በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ከታተመ ደረሰኝ ውጪ በሌላ ማናቸውም ዓይነት ደረሰኝ ወይም ያለደረሰኝ ግብይት ማከናወን እንደማይችል እና ይሄን ካከናወነ ብር 50,000.00 እንደሚቀጣ ያዛል:: በተጨማሪም በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀፅ 19 እና 20 እንዲሁም በታክስ ደረሰኝ አጠቃቀምና አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 149/2011 አንቀጽ 9 በተገለጸው መሰረት ማንኛውም በሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ የመጠቀም ግዴታ ያለበት ተቋም የሽያጭ መሳሪያው በጥገና ላይ ባለበት ጊዜ ካልሆነ በስተቀር በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ከታተመ ደረሰኝ ውጭ በሌላ ማናቸውም ዓይነት ደረሰኝ ማከናወን

እንደማይችል ይገልጻል፡፡ እንዲሁም የፌዴራል መንግስት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት የመንግስት ገንዘብ ክፍያ ቁጥር 9 ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት ሊደረግ የሚገባ ጥንቃቄዎች በንዑስ ቁጥር 7 ለተገዛ ዕቃ ወይም ለአገልግሎት ሂሳብ ሲወራረድ በማስረጃነት መቅረብ ያለበት ሠነዶች በሙሉ ከክፍያው የወጪ ሠነድ ጋር መቅረብ እንዳለበት መመሪያው ያዛል፡፡ በዚህ መሰረት ኢንስቲትዩቱ ለሚፈፅመው ክፍያ ተገቢውን ደረሰኝ የሚቀበል መሆኑን ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ፣

በቀን 30/06/14 በሂሳብ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 208651 በሂሳብ መደብ 6251 ለኩሺቲክ ስቲድዮ ድርጅት በድምር ብር 598,000.00 በሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ የታተመ ደረሰኝ እና በባንክ የተከፈለበት የባንክ ደረሰኝ/አድቫይስ ሳይቀርብ ክፍያ የተፈፀመ መሆኑን በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

3. <u>ለኦዲት ያልቀረቡ የወጪ ሂሳቦች፣</u>

የመቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 982/2008 ክፍል አምስት ንዑስ አንቀጽ 17፣ የተመርማሪዎች ግዴታ በሚለው ርዕስ ስር የፌደራል ዋና ኦዲተር፣ የመሥሪያ ቤቱ ኦዲተሮች ወይም የፌደራል ዋናው ኦዲተር ወኪሎች ለምርመራ ጠቃሚና አስፈላጊ የሚመስሏቸውን መጻሐፍት፣ መዘክሮች፣ መዝገቦች፣ ሰነዶችና ሌሎች የጽሑፍና የቃል መረጃዎች ሁሉ ሲጠይቁ የተጠየቀው ግለሰብ፣ ሠራተኛ ወይም ባለሥልጣን በትክክልና በተሟላ አኳኋን ወዲያውኑ የማቅረብ ግዴታ አለበት ይላል፡፡

በዚህም መሰረት የኢንስቲትዩቱን 2014 በጀት ዓመት የኦዲት ስራ ሲከናወን፡-
በኢንስቲትዩቱ ሰኔ 30/2014 ሂሳብ ሪፖርት ከሚታየው የወጪ ሂሳብ ውስጥ፡-

- በሂሳብ መደብ 6111 እስከ 6133 (የደመወዝና ጥቅማጥቅም ወጪዎች) ብር 77,768,927.42 እና
- በሂሳብ መደብ 6313 ከሚታየው ብር 11,640,307.85 ውስጥ የኤሌክትሮኒክስ እቃዎች ግዥ ወጪዎች ብር 8,320,082.22

በድምር ብር 86,089,009.64 በሰኔ 30/2014 በጀት ዓመት የሂሳብ ሪፖርት ላይ የሚታይ ቢሆንም በኢንስቲትዩቱ መቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 510/2014 መሰረት የደመወዝ፣ጥቅማጥቅም እና የኤሌክትሮኒክስ እቃዎች ግዥ ወጪዎች እንደሚታዩ

ስለሚከለክል የወጪ ሂሳብ ሰነዶችን ኦዲት አድርጎ ትክክል መሆኑን ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

ከላይ ከተራ ቁጥር 1-3 በተገለጹት ጉልህና መሠረታዊ የሆኑ ምክንያቶች የተነሳ በእኛ አስተያየት የኢንስቲትዩቱ የሂሳብ ሪፖርቶች ሰኔ 30 ቀን 2014 ዓ.ም የተመለከተውን የፋይናንስ አቋም እና የበጀት ዓመቱን የሥራ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በትክክል ያሳያሉ በማለት አስተያየት መስጠት አልተቻለም፡፡

ምንም እንኳ ከላይ የተሰጠውን የኦዲት አስተያየት የማይቀይረው ቢሆንም ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ትኩረት ሊሰጣቸው፣ እርምጃ ሊወሰድባቸው እና ለወደፊቱም ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

<u>ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች(Emphasis matter)፣</u>

1. **<u>ያለሂሳብ መደቡ የተመዘገበ የወጪ ሂሳብ፣</u>**

   የፌዴራል መንግሥት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ዓ.ም. በክፍል ሁለት አንቀፅ 6 ተራ ቁጥር 4 ላይ የመንግስት መስሪያ ቤቶች በበጀት አደረጃጀት ሥርዓት መሠረት የተፈቀደላቸው በጀትና የወጣውን ወጪ በሚያሳይ መልኩ ተለይቶ በተሰጠ የበጀት መለያ መደብ ተጠቅመው የሂሳብ እንቅስቃሴያቸውን መመዝገብ እንዳለባቸው መመሪያው ይገልጻል:: በመሆኑም ኢንስቲዩትቱ የወጪ ሂሳቦችን በትክክለኛው የሂሳብ መደብ እየመዘገቡ መሆኑን ለማጣራት ናሙና ተወስዶ ኦዲት ሲደረግ፡-

   በድምሩ 2,375,468.74ብ ትክክለኛ የሂሳብ መደብ መመዝገብ ሲገባው ያለ ሂሳብ አርዕስቱ በሌላ የሂሳብ መደብ/አርዕስት የተመዘገበ መሆኑን በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

2. **በጥራት አረጋጋጭ ኮሚቴ እቃው ተፈትሾ ጥራቱ ሳይረጋገጥ ገቢ የተረደገ እና ክፍያ የተፈጸመበት የእቃን ግዥ በተመለከተ፣**

የፌዴራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 ንዑስ ቁጥር 22 ለ የመንግስት መስሪያ ቤቶች አዲስ ስቶክ ሲቀበሉ በሚከተሉት ላይ ተገቢዉን ማጣራት ማድረግ ይኖርባችዋል በሚለው ስር‹‹የእቃ ግምጃ ቤት ኃላፊዉ የእቃዉን ትክክለኛነት ከተሰጠዉ ትእዛዝ የእቃ ዝርዝር (specification] ጋር በማመሳከር ወይም ባለሞያ የሚፈልግ ከሆነም በባለሞያ ስለትክክለኝነቱ ማረጋገጫ ማግኘት እዳለባቸዉና በፌዴራል መንግስት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል 1 ቁጥር9.2 እና 9.4 ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት ሊደረጉ የሚገቡ ጥንቃቄዎች በሚለው ስር እቃው ወይም አገልግሎቱ በተፈላጊ ባህሪያት ዝርዝር መሰረት መቅረቡን ወይም አገልግሎት መሰጠቱንና አስፈላጊ ሲሆን እቃው ወይም አገልግሎቱ በትክክል ለመቅረቡ ወይም ለመሰራቱ ከሚመለከተው ባለሞያዎች የጽሁፍ ማረጋገጫ መቅረብ እዳለበት ይገልጻል፡፡

ይሁን እንጂ በኢንስቲትዩቱ ለተፈጸሙ ግዥዎች ዕቃዎቹ በታዘዙት ዓይነትና ጥራት ዝርዝር (Specification) መሰረት ለመቅረባቸው በዕቃ ጥራት አረጋጋጭ ኮሚቴ /Technical committee/ የተረጋገጠበት ማስረጃ ሳይቀርብ ተገዝተው ገቢ ለተደረጉ ዕቃዎች ግዥ ብር 3,853,759.32 ክፍያ የተፈፀመ መሆኑን በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡

3. **ስራ ላይ ያልዋለ በጀት በተመለከተ፣**

የፌዴራል መንግሥት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 ክፍል ሶስት አንቀጽ 12(1) ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ለበጀት ዓመቱ የተፈቀደለትን የመደበኛም ሆነ የካፒታል በጀት አጠቃቀም በሚገባ መቆጣጠር እንዳለበት ይገልጻል፡፡ በዚሁ መሰረት ኢንስቲትዩቱ በጀቱን የሚቆጣጠር መሆኑን ለማረጋገጥ የ2014 በጀት ዓመት ለየሂሳብ ኮዶቹ ከተፈቀደው ከ10% በላይ ሥራ ላይ ከዋለው ጋር ሲነጻጸር፣

ከመደበኛ በጀት በድምር ብር 6,433,633.02 ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት መኖሩ በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡

ሌሎች ጉዳዮች (Other Matters)፣

1. **የቋሚና አላቂ የንብረት አያያዝና አጠባበቅ፣**

የንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 ክፍል 4 አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ-መ) በተመለከተው መሰረት አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች ተሰብስበው ስልጣን በተሰጠው የመንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ መሰረት መፈጸም እንዳለበትና በዚሁ መመሪያ አንቀጽ 5 በመንግስት መ/ቤቶች በእጃቸዉ ያለዉን የመንግስት ንብረት በጥንቃቄ የመያዝ፣ የመጠቀም፣ የመቆጣጠር እና አገልግሎት ላይ በማይዉሉበት ጊዜ በወቅቱና በተገቢዉ መንገድ ማስወገድ እንዳለበት ያዛል፡፡ በዚሁ መመሪያ መሰረት ተፈጻሚ መሆኑን የመ/ቤቱ ንብረቶች ኦዲት ሲደረግ፡-

- የእቃ መጋዘን ካለመኖሩ የተነሳ በአንድ የእቃ መጋዘን ዉስጥ ከቀድሞው ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ኢንስቲትዩት የመጡ ንብረቶች፣ የቋሚ እቃ፣ አላቂ እቃ፣ ተመላሽ እቃ፣ የመኪና ቅባቶች እና የሚወገዱ ንብረቶች ለብልሽት በሚዳርግ ሁኔታ በአንድ ላይ ተቀምጠው የተገኙ መሆኑ፡፡
- ያለው የዕቃ መጋዘን ምድር ቤትንፋስ ማስገቢያ (grid) የሌለው በመሆኑ ለክፍሉ ሰራተኞች አስቸጋሪ መሆኑ፣
- በዚሁ መጋዘን ዉስጥ በ2014 ዓ.ም መወገድ ሲገባቸዉ ያልተወገዱ የተለያዩ ላፕቶፕ ብዛት 113፣ ዲስክቶፕ ብዛት 36፣ የተሽከርካሪ ወንበር ብዛት 66፣ የተለያዩ ሀርድ ዲስክ በቁጥር ብዛት 47፣ የእንግዳ ወንበር ብዛት11፣ የኮምፒውተር ጠረጴዛዎች ብዛት 21፣ የተለያዩ ቲቪዎች ብዛት 12፣ ፍሪጅ ብዛት 1፣ የውሀ ማጣሪያ ብዛት 10 ከሚሰሩ ቋሚና አላቂ እቃዎች ጋር በአንድ መጋዘን ዉስጥ የተቀመጡ መሆኑ፣

በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡

2. **የውስጥ ኦዲት በተመለከተ፣**

የፌደራል መንግስት የውሰጥ ኦዲት መመሪያ ቁጥር 7/2003 ክፍል አምስት የውሰጥ ኦዲት ዕቅድና ሪፖርት ማቅረቢያ የጊዜ ሰሌዳ ላይ በንኡስ አንቀፅ 3 በኦዲት ዕቅዱ መሠረት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት እስከ ጥቅምት 30፣ የሁለተኛ ሩብ ዓመት እስከ ጥር 30፣ የሶስተኛ ሩብ ዓመት እስከ ሚያዚያ 30 ድረስ እና የአራተኛ ሩብ ዓመት እስከ ነሐሴ 15 መሆን እንዳለበት ይገልፃል፡፡

- ይሁን እንጂ የውስጥ ኦዲት በጊዜ ሰሌዳ መሠረት የ2014 በጀት ዓመት የውስጥ ኦዲት ሥራ መከናወኑን /መሠራቱን/ በምናጣራበት ጊዜ ወቅቱን ጠብቆ ከአንደኛ ሩብ ዓመት እስከ ሶስተኛ ሩብ ዓመት ድረስ የውስጥ ኦዲት ሪፖርት በተቀመጠለት የጊዜ ሰሌዳ መሠረት የቀረበ ቢሆንም አራተኛ እሩብ ዓመት እስከ ነሃሴ 15 መቅረብ ሲገባው የቀረበው ጥቅምት 15/2015 በመሆኑ በቀረበለት የጊዜ ሰሌዳ ያልወጣ መሆኑን ፤
- የውስጥ ኦዲት በመዋቅሩ የሚያስፈልገው የሰው ኃይል ብዛት 12 ሲሆን ያለው የሰው ኃይል 3(ሶስት) አንድ ዳይሬክተር እና 2 ኦዲተር ብቻ በመሆኑን በሰው ኃይል ያልተሟላ መሆኑን

በኦዲት ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

<u>የህግ ጉዳዮች በተመለከተ(Compliance Issue)፣</u>

4. <u>በውሉ ቀነ ገደብ እቃው ገቢ ባለመሆኑ ያልተቀነሰ የጉዳት ካሳ ቅጣት፣</u>

የፌዴራል መንግስት ሰኔ 2002 ዓ.ም ባወጣዉ የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ክፍል 4 አንቀጽ 16 ቁጥር 16.27.4 ፊደል ሀ-ለ በተገለፀዉ መሰረት ውል የገባው አቅራቢ በውሉ መሰረት አገልግሎቱን በወቅቱ ባለመቅረቡ በውሉ መጠን ላይ 1/1000 ኛ የጉዳት ካሣ የውሉን ጠቅላላ ዋጋ 10% እስከሚደርስ መክፈል እንደሚገባው ይገልጻል፡፡ በዚሁ መመሪያ አንቀጽ 29 ንዑስ አንቀጽ 2 የውል አስተዳደር በሚለው ስር የውል አፈጻጸም የሚከታተለው የመንግስት መ/ቤቱ አካል አቅራቢው በውሉ መሰረት የሚያከናውናቸው ዋና ዋና ተግባራት በውሉ ላይ በተገለጸው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት እየተከናወኑ መሆኑን መከታተል ይኖርበታል ይላል፡፡ በዚህ መሰረት የኢንስቲትዩቱ ውሎች በመመሪያው መሰረት መፈጸማቸውን በናሙና ከተመረጡት ውስጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- በቀን 22/09/2014 ዓ.ም በወጪ ማስመስከርያ ቁጥር 729023 በሂሳብ መደብ 6313 ለኢንስቲትዩቱ በ2014 በጀት አመት ጀነሬተር ግዢ ከኤችቲ ቢኤምኤቲ የኮንስትራክሽን እቃዎች ንግድ በቀን 05/07/14 በብር 920,000.00 ግዥ የፈፀመ ሲሆን በውሉ መሰረት ንብረቱ ገቢ መሆን ያለበት በ29/7/2014 እንደሆነ በውሉ በግልፅ ተቀምጧል፡፡ ነገር ግን ዕቃው ገቢ የሆነው በ29/8/2014 ስለሆነ አቅራቢዉ ንብረቱን ላዘገየበት የ30

ቀን ቅጣት (920,000*30ቀን*1/1000) = ብር 27,600.00 የጉዳት ካሳ ቅጣት ሳይቆረጥ የተገኘ መሆኑ፣

- በቀን 29/8/2014 የሒሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 208945 ለኢንስቲትዩቱ በ2014 በጀት አመት ኮርፖሬት ብራንዲንግ አገልግሎት ለማሰራት ከኩሽቲክ ስቱዲዮ ግዢ በቀን 06/12/2013 በብር 1,196,000 ውል የተያዘና አገልግሎቱ ማለቅ ያለበት በ6/2/2014 መሆን እንዳለበት ውሉ ቢያዝም ነገር ግን ስራው ተሰርቶ እንዳለቀ ማረጋገጫ የተሰጠበት ቀን ግን ከ7 ወር ከ17 ቀን በኋላ በ17/8/2014 በመሆኑ አቅራቢው አገልግሎቱን ላዘገየበት 7ወር ከ17ቀን ወይም 227 ቀናት የጉዳት ካሳ ቅጣት (1,196,000*1/1000*227) = ብር 271,492 ሲሆን፣ ነገር ግን በመመሪያው መሰረት የጉዳት ካሣ የውሉን ጠቅላላ ዋጋ ከ10% መብለጥ ስለሌለበት (1,196,000*10%)=ብር 119,600.00 የጉዳት ካሳ ቅጣት ሳይቆረጥ የተገኘ መሆኑ፣

በድምሩ ብር 147,200.00 ንብረቱን በውሉ መሰረት በወቅቱ ገቢ ባለማድረጋቸው ከአቅረቢዎቹ የውሉን 1/1000ኛ ባዘገዩበት ቀናት የጉዳት ካሳ ቅጣት ሳይቆረጥ ክፍያ የተፈፀመ መሆኑን በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡

2. <u>ያለውድድር በቀጥታ የተፈጸመ ግዥ፣</u>

በፌዴራል መንግስት የግዥና የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 ምዕራፍ 6 አንቀጽ 51 ንዑስ አንቀጽ 1/ሀ መሠረት የመንግሥት መ/ቤቶች ከአንድ አቅራቢ ግዥ መፈጸም የሚችሉት ዕቃው፣ የግንባታ ዘርፍ ስራው፣ የምክር ወይም ተፈላጊው ሌላ አገልግሎት የሚገኘው ከአንድ ዕጩ ተወዳዳሪ ብቻ በመሆኑ ምክንያት ማወዳደር የማይቻል መሆኑ ሲረጋገጥ ነው ብሎ ይደነግጋል፡፡ በተጨማሪም የፌዴራል መንግስት ግዥ አፈፃፀም መመሪያ 2002 መሰረት አንቀፅ 15 ንዑስ አንቀፅ 15/2 እና 15/3 በአዋጁ እና በመመሪያው በተፈቀደው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር የመንግስት መ/ቤቶች ማናቸውም ግዥ በግልፅ የጨረታ ዘዴ መፈፀም አለባቸው፣ የመንግስት መ/ቤቶች ከግልፅ ጨረታ ውጪ በሌሎች የግዥ ዘዴዎች ግዥ መፈፀም የሚችሉት በአዋጁና በዚህ መመሪያ ላይ ተመስርቶ እንደሚከናወን ይገልፃል፡፡ ኢንስቲትዩቱ ግዥዎችን በመመሪያው መሰረት እያከናወነ መሆኑን <u>ለማረጋገጥ የግዥ</u> ወጪዎች ናሙና ተወስዶ ኦዲት ሲደረግ፡-

በቀን 29/8/2014በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 209097 በሂሳብ መደብ 6313 ብር 176,704.00 የቢሮ እቃዎች ያለውድድር በቀጥታ ከኩዊንስ ሱፐርማርኬት ግዥ በማከናወን ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

3. <u>በጨረታ መገዛት ሲገባው በመከፋፈል በዋጋ ማወዳደሪያ የተፈጸመ ግዥ፣</u>

በፌዴራል መንግሥት የግዥና የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀፅ 33 ቁጥር 4 በዚህ አዋጅ ወይም በግዥ መመሪያው የተዘረጉ የግዥ ስርዓቶችን ለማሻሻል የመንግስት መ/ቤቶች በአንድነት መፈጸም የሚገባቸውን የእቃ፣ የግንባታ ወይም የአገልግሎት ግዥዎችን መከፋፈል የለባቸውም ይላል፡፡

ይሁን እንጂ ኢንስቲትዩቱ አስቀድሞ ማቀድ እስከተቻለ ድረስ በአንድ ላይ ሊፈጸሙ የሚገባቸውን የእቃና የአገልግሎት ግዥዎችን በግልጽ ጨረታ የግዥ ዘዴ መፈጸም ሲገባ የተለያዩ የብረት መደርደሪያዎች እና የተለያዩ የቢሮ ወንበሮች በመከፋፈል በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ ድምር ብር 2,824,508.92 ግዥ በማከናወን ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

4. <u>በግልጽ ጨረታ መገዛት ሲገባው በዋጋ ማወዳደሪያ የተገዛ ግዥ</u>

በፌዴራል መንግሥት የግዥና የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀፅ 51 ንዑስ አንቀጽ 1/ሀ የመንግስት መ/ቤቶች ከአንድ አቅራቢ ግዢ መፈጸም የሚችሉት እቃው ወይም አገልግሎቱ የሚገኘው ከአንድ እጩ ተወዳዳሪ ብቻ በመሆኑ ምክንያት ማወዳደር የማይቻል መሆኑ ሲረጋገጥ እንደሆነ ተገልጿል፡፡ እንዲሁም ሰኔ 2002 የወጣው የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ክፍል 4 አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ 2 በአዋጅና በመመሪያው በተፈቀደው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር የመንግስት መ/ቤቶች ማናቸውንም ግዥ በግልፅ የጨረታ ዘዴ መፈጸም እንዳለባቸው ያዛል፡፡ በተጨማሪም የገንዘብ ሚንስቴር በቀን 25/01/2014 ባወጣው የግዥ ማሻሻያ መመሪያ በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ መገዛት ያለበት ለዕቃወች እስከ ብር 400,000 እንደሆነ ተገልጿል፡፡ኢንስቲትዩቱ በመመሪያው መሰረት ግዥን ያከናወነ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ፣

- የተለያዩ የህትመት እቃዎች ግዥ ብር 1,408,557.77
- ለዳታ ሴንተር ምርቃት የህትመትና የቁሳቁስ ግዥ ብር 1,090,073.00

በድምሩ ብር 2,498,630.77 በግልጽ ጨረታ የግዥ ዘዴ መፈጸም ሲገባው በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ ከኩሽቲክ ስቱድዮ አድቨርታይዚንግ ወርክ ከተባለ ድርጅት ግዥ በማከናወን ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

- በተጨማሪም ኢንስቲትዩቱ ከላይ ከተጠቀሰው ድርጅት በተደጋጋሚ ግዥ የሚፈጽም መሆኑ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

5. <u>በግዥ ዕቅዱ መሰረት ያልተፈጸመ ግዥ፣</u>

በፌዴራል መንግስት የግዥ እና የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀጽ 22 ንኡስ አንቀጽ 1 እና 2 እንዲሁም በግዢ አፈጻጸም መመሪያ አንቀጽ 13 መሰረት የመንግስት መ/ቤቶች የግዢ እቅድ በማዘጋጀት የቀጣይ በጀት አመት ዕቅዳቸውን በመ/ቤት የበላይ ሀላፊዎች ጸድቆ ለግዥ እና ንብረት ባለስልጣን በማቅረብ የግዢ አፈጻጸሙም በመመሪያው አንቀጽ 15.2 መሰረት በአዋጁና በመመሪያው በተፈቀደው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር የመንግስት መ/ቤቶች ማናቸውንም ግዥ በግዥ ዕቅዱ መሰረት በግልጽ ጨረታ መፈጸም እንደሚገባ ይገልጻል፡፡በተጨማሪም በቀን 17/8/2014 የመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን ባወጣው ሰርኩላር መመሪያ መሰረት ከሚያዝያ 30 ቀን 2014ዓ.ም በኃላ በቀሩት ሁለት ወራቶች ውስጥ ግዥ መፈጸም እንደሌለበት ይገልጻል፡፡ በዚህም መሰረት ከተመረጡ ወጪዎች በናሙና ኦዲት ሲደረግ፣

ኢንስቲትዩቱ በግዥ እቅዱ ላይ ያልተካተቱ የተለያዩ ግዥዎችን ከመመሪያ ውጭ በግንቦት እና በሰኔ ግዥ በማከናወን በድምሩ ብር 2,148,717.96 ክፍያ የተፈጸመ መሆኑን በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

6. <u>በወቅቱ ያልተወራረዱ ተከፋይ ሂሳብ፣</u>

የፌደራል መንግስት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ ሀ ማናቸውም ክፍያ የሚፈጸምባቸው ሂሳቦች ተከፋይ ሂሳብነታቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ሲቀርብና ስልጣን ባለው አካል ሲፈቀድ ብቻ በተከፋይ ሂሳብ መያዝ እንዳለበት እንዲሁም አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 5/ሐ የተለያዩ አካላት ቀንሰው ያስቀሩትን የግብር እና ሌሎች ሂሳቦች ለሚመለከተው ግብር አስገቢ አካል ወቅቱን ጠብቀው ማስተላለፍ እንዳለበት ያስቀምጣል፡፡ ኢንስቲትዩቱ በመመሪያው መሰረት የተከፋይ ሂሳቦችን ለመከታተል ተገቢው የቁጥጥር ስርዓት መዘርጋቱንና ተከፋይ

ሂሣቦችን በገባው ግዴታ መሰረት በወቅቱ የሚከፍል መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

ኢንስቲትዩቱ የሰኔ 30/2014 በጀት ዓመት የሂሳብ ሪፖርት ላይ በሂሳብ መደብ 5054 (other Deposit t) የአደራ ሂሳብ ብር 145,603,934.66 ከ1995-2014 ዓ/ም ጀምሮ በወቅቱ ለባለመብቶቹ መከፈል ሲገባው ያልተከፈለ ውዝፍ የተከፋይ ሂሳብ መኖሩ በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት